የሰ/መ/ቁ. 34703

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች**:- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**:- እንደሻው ፍቃዱ - ቀረበ፡፡

**ተጠሪዎች**:- እነ ወንድማገኝ ፍቃዱ /ሰባት ሰዎች/

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ አመልካቹ በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተው ይዘውት ከሚገኘው የውርስ ንብረት ድርሻውን እንዲያካፍሉት ነው፡፡ ከተጠሪዎች መሃል ስድስቱ ለክሱ በሰጡት መልስ ከሣሹ ልክ እንደኛው ወራሽ ነው፤ ድርሻውን ለማካፈል ዝግጁ ነን፤ በእርግጥ የጠየቀው የውርስ ሃብት ግምት የተጋነነ ነው በማለት ሲከራከሩ አንዱ ደግሞ ጉዳዩ በሽምግልና እየታየ ነው የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩ ውርስን የሚመለከት በመሆኑ ከሣሽ የውርስ ሃብቱ ይጣራልኝ የሚል ክስ በቅድሚያ ሊያቀርብ ይገባል የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ሰርዟል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ብይን ጉድለት የለበትም ብሏል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ታሕሣሥ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የውርስ ማጣራት ስርዓት አልተካሄደም በሚል ምክንያት አመልካች ያቀረበው የውርስ ሃብት ልካፈል ክስ ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው በአመልካች የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ግልጽ ነው፡፡ ክሱን የመሠረተው በወንድሞቹ እና እህቶቹ ላይ ሆኖ በወራሾች መካከል ካልተከፋፈለው የሁሉም አባት ንብረት ላይ የውርስ ድርሻውን እንዲያካፍሉት ነው፡፡ የክፍያ ጥያቄ ያቀረበባቸውን የውርስ ሃብቶችም /ንብረቶች/ በክስ ማመልከቻው ላይ ዘርዝሮ ስለማቅረቡ አቤቱታ በቀረበበት ብይን ላይ ተመልክቶአል፡፡ አመልካች ተጠሪዎችን የከሰሰበት ምክንያትም ግልጽ ነው፡፡ ይኸውም የውርስ ሃብቶቹን በእጃቸው ይዘው ስለሚገኙ ነው፡፡ ተጠሪዎች ለስር ፍ/ቤትም ሆነ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት መልሳቸው ንብረቶቹን አልያዝንም /በእጃችን አይገኙም/ የሚል ክርክር አላነሱም፡፡ አመልካች ወራሽ አይደለም ወይም ከተባሉት ንብረቶች የሚያገኘው መብት የለም የሚል ክርክርም የላቸውም፡፡ ይልቁንም በክሱ የተጠየቀውን በመቀበል ለአመልካች ድርሻውን ለማካፈል ዝግጁ መሆናቸውን ነው የገለጹት፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ ጉዳይ ወራሾቹም ሆኑ የውርስ ሃብቶቹ በግልጽ ተለይተው ታውቀዋል፡፡ ሳይከናወን የቀረው ንብረቶቹን በወራሾቹ መካከል የመከፋፈሉ ጉዳይ ነው፡፡ በእርግጥ ከውርሱ ሃብት የሚከፈል ዕዳ እንዳለና በአመልካች ክስ የተመለከተው የንብረት ግምት የተጋነነ እንደሆነ በተጠሪዎች ክርክር ተገልጾአል፡፡ እንደተባለው ከውርስ

ሃብቱ ላይ የሚፈለግ ዕዳ ካለ ክሱ በቀረበበት ፍ/ቤት መሪነት በማስረጃ ተጣርቶ ሊታወቅ የሚችል ነው፡፡ ተጠሪዎችም በእርግጥ ያልተከፈለ እና በትክክልም ከውርስ ሃብቱ ላይ የሚከፈል ዕዳ አለ ካሉ ይህንኑ በማስረጃ አስረግጠው ለፍ/ቤቱ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን ዕዳ አለ በመባሉ ምክንያት ሕግና ስርዓት ተከትሎ የቀረበው ክስ የሚዘጋበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡

አመልካች ክስ በመሠረተበት /ለክሱ መነሻ በሆነው/ ሃብት ላይ ጥቅም ወይም መብት እንዳለው አረጋግጦ ነው /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 33/፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በጉዳዩ ላይ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የለውም አልተባለም፡፡ ፍ/ቤቱ ክሱን የሰረዘው የዳኝነት ስልጣን የለኝም በሚል ቢሆንም፤ ለዚህ የሰጠው ምክንያት ግን የውርስ ማጣራት ስርዓት አልተካሄደም የሚል ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የውርስ ሃብት ክፍፍልን መነሻ የሚያደርግ ክስ በውርስ አጣሪ በኩል ካላለፈ በቀጥታ ወደ ፍ/ቤት አይቀርብም የሚል አስተሳሰብ ወይም አካሄድ የተያዘ መሆኑን ነው፡፡ በእርግጥ በወራሾች በራሳቸው ወይም በተመረጠ በሌላ ሰው አማካይነት ውርስ እንደሚጣራ በሕጉ ተመልክቶአል፡፡ ከውርስ ማጣራት ተግባራት አንዱ የውርስ ሃብቱን መከፋፈል እንደሆነም ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ይህ እንግዲህ አንዱ የውርስ ሃብት የሚከፋፈልበት መንገድ ነው ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ድርሻዬን አላገኘሁም የሚል ወራሽ የውርስ ሃብቱን በያዘው ሰው ላይ በቀጥታ ክስ የመመስረት መብት የለውም ወይም ሕጉ ከልክሎአል ለማለት የሚቻል እንዳልሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የውርስ ሃብቶቹ በተጠሪዎች እጅ ተይዘው እንደሚገኙ አላከራከረም፡፡ አመልካችም ከእነዚህ ሃብቶች ላይ ድርሻውን እንዲያገኝ ነው የጠየቀው፡፡ በመሆኑም እንደማንኛውም የፍትሐብሔር ክርክር ታይቶ እና በማስረጃ የሚጣራ ካለም ተጣርቶ ሊወሰን ሲገባ የውርስ ማጣራት ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ ተደርጎ መወሰዱ ትክክል አይደለም፡፡ ፍ/ቤቱ የዳኝነት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 49517 ሐምሌ 10 ቀን 99 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 32508 ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከፈተው መዝገብ በመቀጠል በግራ ቀኝ ወገኖች የሚቀርብለትን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኂላ የመሰለውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሠረት ይመለስለት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ